# *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

## ሕዋሶቻቸንን / ልቦናችንን በሥራ ማስለመድ (getting our senses exercised by reason of use)

ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው (have their senses exercised by reason of use) ለፍጹማን ሰዎች ነው።

# ክፍል አራት: መስማት/ ማድመጥ

አመንኩ ስለዚህም ተናገርኩ... [መዝ (116):1]

እምነት ከመስማት ነው: መስማትም በእ/ር ቃል ነው.... [ሮሜ 10:17]

ቁጥር13-17
እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም። ኢሳይያስ። ጌታ ሆይ፥ ምስክርነታችንን ማን አመነ? ብሎአልና። እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

የምናየው ወይንም የምንናገረው ነገር ብቻ ሳይሆን የምንሰማውም ነገር እኛን የመቆጣጠር ሃይል እንዳለው ማወቅ አለብን::

**ምን/ እንዴት እንስማ?**

ማር 4:23-25 (ሙሉውን ምዕራፍ ይነበብ)
የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ። አላቸውም። ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ። በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል። ላለው ይሰጠዋልና፤ ከሌለውም ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።
(ይህ ከማቴ 7:2 የተለየ ቃል ነው)

Amplified Version
24And He said to them, Be careful what you are hearing. The measure [b][of thought and study] you give [to [c]the truth you hear] will be the measure [d][of virtue and knowledge] that comes back to you--and more [besides] will be given to you who hear.

ሉቃ 8:17-18
የማይገለጥ የተሰወረ የለምና፥ የማይታወቅም ወደ ግልጥም የማይመጣ የተሸሸገ የለም።እንግዲህ እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ፤ ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና፥ ከሌለውም ሁሉ፥ ያው ያለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል።

Amplified Version
18Be careful therefore how you listen. For to him who has [spiritual knowledge] will more be given; and from him who does not have [spiritual knowledge], even what he thinks and [a]guesses and [b]supposes that he has will be taken away.

ዛሬ የምንኖረው ምናልባትም ከምንጊዜውም በላይ ጩኸት በበዛበት ዘመን ላይ ነው:: (imagine: አዲስ አበባ ታክሲ ተራ ወይንም መርካቶ እንደቆማችሁ አይነት)

- ማን እንደሆንን ሊነግሩን የሚደፍሩ ጋዜጣ የሚያሳትሙበት (..."ኮኮባችንን" እየቆጠሩ: መዳፋችንን እያዩ...)
- ለልጆቻችን ከእኛ ይልቅ እነርሱ እንዳሉላቸው/ ወይንም እንደሚያውቁላቸው በመዋዕል ሕጻናት ሳይቀር ትምህርት በሚሰጡበት
- በአጠቃላይ የየእለቱ ውሎአችንን ለመቆጣጠርና ከተቻለም የሕይወታችንን ምርጫና ውሳኔ በሚፈልጉት መልክ ለመቃኘት ከየአቅጣጫው የሚደረግብን ዘመቻ ቀላል አይደለም::

**ታዲያ ማንን እንስማ? መስፈርቱ ምን መሆን አለበት?**

## *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

1) ስለእኛ ፈጽሞ የሚያውቀውን እንስማ
   - ሰሪ የእጁን ስራ እንደሚያውቅ ስለእኛ/ን ራሳችንን ካወቅነው ይልቅ አብልጦ የሚያውቀን የሠራን እርሱ ብቻ ነው::

   "<u>በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ</u>፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ።" ኤር 1:5
2) እውነት የሆነውን ብቻ የሚነግረንን እንስማ
   - በእውነት ሁሌ ደስ የሚለው፣ እውነት የሆነውን ከመናገር ማንንም ፈርቶ የማይመለሰው፣ በእውነት ካልሆነ እርሱ ራሱ የማይገኝ እርሱ ብቻ ነው::

   "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር...።" ዮሐ 14:6
3) ስለ እኛ ሁሌ መልካም የሚያስበውን እንስማ
   - መልካም እንጂ ክፉ ከእርሱ የማይገኝ፣ ለወጉት እንኳን ይቅርታን የሚለምን፣ ስለጠላቶቹ ራሱን የሚሰጥ እርሱ ብቻ ነው::

   "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።" ኤር 29:11

   "እግዚአብሔር መልካም ነው፥ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል።" ናሆ 1:7

እነዚህን በከፊል የሚያሟሉ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል:: ሁሉን ማሟላት የሚችል ግን ሊሰማ የተገባው እ/ር ብቻ ነው::

## <u>እ/ርን መስማት</u>

ለብዙ ሰዎች ትልቁ ጥያቄ "የእ/ርን ድምጽ እንዴት እንለይ?" / ወይንም "የእ/ርን ፈቃድ እንዴት እንወቅ" የሚል ነው":: ስለዚህ ጉዳይም ብዙ ቲዎሪዎችንም ሰምተናል::

በእርግጥም እ/ር መንፈስ ስለሆነ በአካላዊው አለም ውስጥ ለሚኖር ሰው እ/ርን መስማት የሚታሰብ ነገር አይደለም:: ሆኖም መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዳግም በተወለደ መንፈሱ ከእ/ር ጋር መነጋገር

ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ <u>በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል</u>፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ <u>በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል</u>፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፥ <u>የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና</u>። ዮሐ 10:

የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ <u>ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ</u>። ሮሜ 12:2

ፈትኖ ማወቅ / መለየት አንድ አይነት የብስለት ደረጃን የሚያመለክት ሲሆን ይህ ብቃት በሂደት ሊዳብር የሚችል ነገር እንደሆነ ቃሉ "...በልባችሁ መታደስ" ሲል ያሳየናል፤ ተሃድሶ ሂደት ነውና::

**ስለዚህ ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው የእ/ር ድምጽ አንዳንድ ጊዜ ግራ ሲጋባን ወይንም ምሪት ስንፈልግ ብቻ የምንፈልገው ሳይሆን የአዲሱ ውልደት የማያቋርጥ የሕይወት ሥርዓት ነው::**
**እግዚአብሔር ሁልጊዜ በሥራ ላይ እንደሆነ ሁሉ ሁልጊዜ ደግሞ እየተናገረ ነው::**
**አንዳንድጊዜ "እ/ር ዝም አለ" ወይንም "የእ/ር ድምጽ ጠፋ" እንደሚባለው አይደለም! ወይንም እንደዔሊ ዘመን ቃሉ "ብርቅ" ራዕይም የማይገለጥበት ዘመን አይደለም!**

- እርሱ already በተጻፈው ቃሉ ሃሳቡን ሁሉ ተናግሯል
- በቅዱስ መንፈሱ በኩል ደግሞ የተጻፈ ቃሉን ይገልጸዋል

**ማን ነው እ/ርን የሰማ? ሊሰማ የሚችል? የማይሰማስ?**
**በ"ጌታ ተናገረኝ"... ሰበብ ብዙ ነገር ጠፍቷል**

## *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

XX በራሱ ምኞት ተይዞ የእ/ርን ምሪት/ ድምጽ ሊሰማ የሚፈልግ? XX

XX "አዋቂ" - ብዙ ያለው / የሚያውቅ የሚመስለው XX

1) ሰምቶ የሚያስተውለው
ሉቃ 8:10
እርሱም እንዲህ አለ፦ ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ ለሌሎች ግን እያዩ እንዳያዩ እየሰሙም እንዳያስተውሉ በምሳሌ ነው።

2) ሰምቶ የሚያደርገው
ያዕ 1:22-25

**እ/ርን መስማትን ራስን ማስለመድ**

1) ዝም ማለትን / የልባችንን ምኞትና ፈቃድ ጸጥ ማሰኘትን እንማር
ጌታ ኢየሱስ አባቱን እንዴት ይሰማ ነበር?
ዮሐ 5:30 እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።

**ጠቃሚ ምክር:- በጣም የተናደድህ/ሽ ወይንም የከፋህ/ሽ ቀን ውሳኔ አትወስን/ኚ!**

2) የድምጹን ባሕሪይ እንወቅ

1ነገሥት 19:11-12
እርሱም፦ ውጣ፥ በተራራውም ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቁም አለ። እነሆም፥ እግዚአብሔር አለፈ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ ዓለቶቹንም ሰባበረ፥ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም። ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም። ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም። ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ።

ይህ ክፍል እ/ርን ለመስማት እንደካሪዝማቲካዊ ባህል ያለውን ምክንያት አልባ ስሜታው ነውጥን የመፈለግን ዝንባሌ የሚቃወም ነው::

3) እ/ርን እንወቅ ድምጹንም እናውቃለን

ቀድሞ እንደልጅ እናስብ፣ እንደልጅ እናይ፣ እንደልጅ እንናገር ነበር

ከሁሉ በላይ ግን:-
"...እርሱ የሚላችሁን አድርጉ"